የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እነ መለስ ያቀረቡላቸውን የእራት ግብዣ ሳይቀበሉት ቀሩ

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና ጃሌዎቹ በኮንዶሊዛ ራይስ ድርጊት ተበሳጭተዋል

ውጭ ጊዳይ ሚኒስትሯ መለስ ባልተገኘበት የአምስቱ ሐገራት መሪዎች ጋር ዝግ ስብሰባ አደረጉ

አዲስ አበባ ከ3ሺህ በላይ የወያኔ ካድሬዎች ሊረከቡዋት ነው

ለዘመናት ተቀምጦ የነበረው የቤተክህነት ቅርስ ወደ አክሱም ተጫነ

አባ ገ/መድህን ፎቶዋቸው በየአደባባዩ እንዲሰቀል ጥበቅ ትዕዛዝ ሰጡ

የወያኔ የፌዴራል ፖሊሶች አለቆቻቸውን አማረሩ

የበረከት ተላላኪ የሆነው ግለሰብ አፋኙ የፐሬስ ሕግ እንዲፀድቅ ለማድረግ እየተሯሯጠ መሆኑ ተጋለጠ የሚሉ እና ሌሎችም ይገኙበታል

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስ በኢትዮጵያ ለሁለት ቀን የስራ ጉብኝት ያደርጋሉ ተብሎ ረቡዕ ሕዳር 25 ቀን 2000 ዓም ከጧቱ ሁለት ሰዓት ላይ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሰዋል።

በዚሁ ዕለት የውጭ ገዳይ ሚኒስትሯን ለመቀበል መለስ ዜናዊ ወይም ስዩም መስፍን ይገኛል ተብሎ የተጠበቀ ቢሆንም በውል ተለይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስር የፕሮቶኮል ሹም የሆነ ግለሰብ የተቀበላቸው ሲሆን፣ በዚህ ድርጊት በመናደዳቸው የቤተመንግስት እንግዳ መቀበያ መኪኖችን አልፈልግም በማለት በአሜሪካ ኤምባሲ መኪና ለመጓዝ እንደቻሉ ለማወቅ ተችሏል።

የፈራረሰች ሐገር ሱማሊያ ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር መጡ ተብሎ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ደማቅ አቀባበል ያደረገላቸው ሲሆን የጌቶቹን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሌዛ ራይስ ሲመጡ እራሱ ያልተቀበለ ከመሆኑም ባሻገር ሌሎቹም ባለሥልጣናት እንዳይቀበሉ መደረጉ ከሴትዬዋ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሻከረ መሆኑን ያመላክታል ያሉት አንዳንድ ዲፕሎማቶች ኮንዶሊዛ ራይስ በዚህ በወያኔ መሪዎች ድርጊት ከመናደዳቸው የተነሳ ያለ አንዳች አጃቢ በራሳቸው ዜጎች በአሜሪካ ኤምባሲ አምባሳር ዶናልድ ያማማቶ እና በአፍሪካ ሕብረት የአሜሪካ አምባሳደርና ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ የአሜሪካ ዜጎች ብቻ አቀበባበል እንደተደረገላቸው ለማወቅ ተችሏል።

ጥይት በማይበሳው የአምባሳደሩ መኪና እና ሌሎች ሶስት ተመሳሳይ ቼቭሮሌት መኬኖች የተጓዘት ኮንዶሊዛ ራይስና አምባሳደሮቹ ከታላላቅ ሐይቆች ባለቤት ሐገሮች ከሆኑት መሪዎች ጋር ለመወያየት ወደ ኤምባሲው በቀጥታ እንደተጓዙ ታውቋል።

ቀደመው አዲስ አበባ የደረሱት የብሩንዲው፣ የሩዋንዳው፣ የኮንጐው እና የኡጋንዳው ፕሬዝዳንቶች በተገኙበት በአሜሪካ ኤምባሲ ዝግ ስብሰባ ያካሄዱ መሆኑን የዲፕሎማቲክ ምንጮች ገልፀው በተለይም በታላላቅ ኃይቆች ዙሪያ ያለውን የሠላም ሁኔታና በዳርፉር ስላለው ችግር እንዲሁም ወደ ሱማሊያ ጦር ለመላክ ስላላቸው እቅድና ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት አሜሪካም በጦር መሣሪያና በገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን በዝግ ስብሰባው ላይ የተነሱ አጀንዎች መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል።

ይህንን ዝግ ስብሰባ ከጨረሱ በኋላ በ8 ሰዓት ላይ የአራቱ ሐገራት ፕሬዝዳንቶችና ኮንዶሊዛ ራይስ በጋራ በመሆን ስለተወያዩበት ጉዳይ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡ ሲሆን፣ በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይም ሁሉም ፕሬዝዳንቶች በታላላቅ ኃይቆች ዙሪያ ሠላም እየሰፈነ መሆኑን ገልፀዋል።

ከወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና ከወያኔው ባለስልጣን ስዩም መስፍን ጋር ሰፊ ውይይት ይደረጋል ተብሎ የተጠበቀ ቢሆንም ከ30 ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ

እንዳነጋገሯቸው ዲፕሎማቶቲክ ምንጮቹ ገልፀው በተለይም የአቀባበሉ ጉዳይ እጅግ ያንገበገባቸው በመሆኑ ቀሪውን ቀሪውን ጊዜያቸውን በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደርና በአፍሪካ ሕብረት የአሜሪካ አምባሳደር ከሆኑት ወ/ሮ ጋር ብቻ በውይይት ያሳለፉ መሆኑን የጠቀሱት ምንጮቹ የወያኔው መሪዎች የጌቶቻቸውን መልዕክተኛ በአግባቡ ያለመቀበላቸው ተስፋ ከመቁረጥና ከእንግዲህ ምን ያመጡብናል ከሚል በመነጨ መልኩ ሳይሆን እንዳልቀረም ግምታቸውን ይሰነዝራሉ።

በተጓዳኝ ከቤተመንግስት እንግዳዋን ለመቀበል የተጓዙትን መኪኖች አልፈልግም በማለት በራሳቸው ኤምባሲ መኪና መጓዛቸው እነ ወዲ ዜናዊን ያገበገበና ያቃጠላቸው ሲሆን፣ ረጅም ሰዓት ሰጥተውን ያወያዩናል ብለው ተስፋ አድርገው ሲጠባበቁ የነበረ ቢሆንም ከ30 ደቂቃ ላልበለጠ ጊዜ ብቻ የሠላምታ ያህል ማነጋገራቸው ተጨማሪ ለነ ወዲ ዜናዊ ብሽቀትና ብግነት የፈጠረባቸው መሆኑን የገለፁት የዲፕሎማቶቲክ ምንጮች በተለይም የእራት ግብዣ ተዘጋጅቶላቸው የነበረውን ፕሮግራም መሰረዛቸው ከምንም በላይ ለወያኔ መሪዎች የሞት ሞት መሆኑት አስምረውበታል።

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ከወያኔ ቴለቭዥን ጋዜጠኛ ስለ ኤች አር 2003 ተጠይቀው «ይህ የአሜሪካ አቋም አይደለም» በማለት በሚያሻማ መልኩ የሰጡ ከመሆኑም በተጨማሪ አጭር ምላሽ በመስጣቸው ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠት አለመፈለጋቸውን ያሳያል ያሉት ምንጮች ለራይስና ለአለቆቿ ትልቅ እና አንገብጋቢው ጉዳይ የሱማሊያ፣ የዳርፉር እና በታላላቅ ኃይቆች ዙሪያ ያለው የሠላም ሁኔታ መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስ ከአውሮፕለን ማረፊያ ከደረሱ ጥቂት ደቂቃዎች ተከትሎ የኡጋንዳው ፕሬዝዳንት ፖል ካጋሜ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የደረሱ ሲሆን፣ እሳቸውም በተመሳሳይ መልኩ ተራ የፕሮቶኮል ሹም የሆነው ግለሰብ አቀባበል ያደረገላቸው ሲሆን፣ ሌላ አንደም ሚኒስትር ወይም ባለሥልጣን በስፍራው አልተገኘም።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ኮንዶሊዛ ራይስ ከአራቱ የአፍሪካ መሪዎች በተጨማሪ ከሱማሊያ ጠ/ሚ/ር ኑር ሁሴን ሐሰን ጋርም ውይይት ያደረጉ ሲሆን፣ በዚህ በውይይታቸው ላይ ፍፁም አክራሪ ካልሆኑ እና ለዘብተኛ ከሆኑት የሱማሊያ የሽግግር መንግስት ተቃዋሚዎች ጋር ድርድር እንዲደረግና አዲስ ሕገ መንግስትና የምርጫ ሕግ ማፅደቅን ጨምሮ መፈፀም ያለባቸውን ጉዳዮች ለማከናወን የጊዜ ሰሌዳ እንዲያወጡና ተግባራዊ እንዲያደርጉ መመሪያ መስጠታቸውን ታውቋል።

ሁለቱ ባለስልጣናት ባካሄዱት ውይይት ላይ የአፍሪካ ሕብረት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወካዮች የተገኙ ሲሆን፣ በሱማሊያ ለተፈጠረው ቀውስ የአፍሪካ

ሕብረት ጦር በአስቸኳዋይ ልኮ አካባቢውን ሠላም ማስፈን እንዳለበትና የወያኔው ጦር ከሱማሊያ እንዲወጣም መመሪያ እና ትዕዛዝ መስጠታቸውም ተጠቁሟል፡፡

እንደ ለቅሶ ደራሽ ለ30 ደቂቃ ብቻ የሕወሓቱን ሊቀመንበር መለስ ዜናዊን እና የሕወሓቱን ምክትል ሊቀመንበር ስዩም መስፍንን አነጋግረው የወጡት ኮንዶሊዛ ራይስ በሱማሊያ፣ በሱዳንና በኤርትራ በኩል ስላለባቸው ችግር አስቸኳዋይ መፍትሄ መስጠት እንዳለባቸው አሳስበዋቸዋል፡፡ በተለይም ከኤርትራ ጋር የጀመሩት ፍጥጫ በአስቸኳዋይ መርገብ እንዳለበትና በግንባሩ ዙሪያ ያለውን ውጥረት ለማርገብ ተጨባጭ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ለሕወሓቶቹ ሹማምንቶች ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውንም ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ የዲፕሎማቲክ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በታችኛው ቤተመንግስት ውስጥ ከሰዓት በኋላ ሁለቱን የሕወሓት ባለሥልጣን አንድ ላይ ያነጋገሩት ራይስ ከ30 ደቂቃ ላልበለጠ ገዜ ቆይታ ያደረጉ ሲሆን፣ ምሽት ላይ በቤተመንግስት የእራት ግብዣ ቢደረግላቸውም ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ የእራት ግብዣውን የሰረዙ ሲሆን፣ በተለይም የሕወሓቶቹን ባለሥልጣን ለረጅም ሰዓት ያነጋገሯቸዋል ተብሎ ሲናፈስ ቢቆይም እንደ ለቅሶ ደራሽ ሁለቱን አንድ ላይ ማነጋገራቸውም በወያኔና በአሜሪካ መካከል ምን ተፈጥሮ ይሆን? የሚል ጥያቄም እያስነሳ ይገኛል፡፡

ለ24 ሰዓት በአዲስ አበባ ቆይታ ያደረጉት ኮንዶሊዛ ራይስ ሕዳር 26 ቀንከጧቱ 2 ሰዓት ላይ ወደ ቤልጅየም ብራሰልስ እንደተጓዙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሱማሊያው አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኑር ሐሰን ከኮንዶለዛ ራይስ ጋር ወይይት ካደረጉ በኋላ በሰጡት መግለጫ የሽግግር መንግስቱ ቆይታ ጊዜ 5 ዓመት መሆኑን ገልፀው 3 ዓመቱ ያለምንም ውጤት ያለፈ ቢሆንም በቀሩት ዓመታት ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ለማድረግ ሙከራ አደርጋለሁ ብለው መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ምንም እንኳዋን አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ይህን የ የመሰለ መግለጫ ቢሰጡም እሳቸው ከተሾሙ በኋላ እንኳዋን 5 የካቢኔ አባላት ስራቸውን ለቀው እንደወጡ የገለፁት ምንጮች አሁን በሱማሊያ የሽግግር መንግስት ውስጥ ያለው ችግር ሊቀረፍ እንደማይችል አመላካች ነው ሲሉም ያላቸውን ግምት ይሰነዝራሉ፡፡

የሱማሊያ የሽግግር መንግስት ፕሬዝዳንት አብዱላሂ ዩሱፍ ባደረባቸው ሕመም በኬንያ በሕክምና ላይ የሚገኙ መሆኑም ታውቋል፡፡

በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ጉዳዮች ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሣራ እየደረሰበት ያለው ወያኔ በሕዳር 24 ቀን 2000 ዓም በተወካዮች ም/ቤት በተደረገ ስብሰባ ላይ ሌላ የፖለቲካ ኪሣራ እንደደረሰበትም ከምክር ቤት ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ፡፡

በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ የቀበሌና የሚሚያ ምርጫ ለማድረግ በሚል በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ በቂ ውይይት ሳይደረግበት ወያኔ በግዴታ ማፅደቁም ታውቋል፡፡

ለአዲስ አበባ ም/ቤት 139 ወንበሮች የም/ቤት አባሎች እንዲኖሩት የሚያትተው ይኸው ረቂቅ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ 300 ተመራጮች እንዲሾሙ በሚል ያፀደቀ ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ ተመራጭ ከ1000 ብር በላይ ደመወዝ ተከፋይ እንደሚያደርግም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ያስረዳል፡፡

በአሁን ሰዓት በአዲስ አበባ 10 ክፍለ ከተሞች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ክፍለ ከተሞች ስር ደግሞ 99 ቀበሌዎች እንዳሉ የሚታወቅ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች በአዲስ አበባ ባሉት ቀበሌዎች ውስጥ የሚሰሩ የወያኔ ካድሬ ተመራጭ ተብዬዎች ከ3000 በላይ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል ብለዋል፡፡

ዛሬ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሚልሰውና የሚቀምሰው አጥቶ በኑሮ ውድነት እየተጠበሰ ባለበት በዚህ ወቅት ተመራጭ ናቸው በሚል ሰበብ የወያኔ ጆሮ ጠቢዎችን በየቀበሌው ለመበተን በዝግጅት ላይ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች ለአንድ ቀበሌ ከ30 በላይ የም/ቤት አባሎችን በማስቀመጥ ለደህንነት ሥራ እንዲሰሩ ለማድረግና ሕዝቡን በጐጥና በቡድን ከፋፍሎ ለመቆጣጠር ሆን ተብሎ የታቀደ ሲሆን እያንዳንዱ ተመራጭ ተብዬ የደህንነት አባል ከ1000 ብር በላይ ተከፋይ ደመወዝ ያለው መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች በወር ከ300 ሺህ ብር በላይ ደመወዝ ብቻ የሕዝብ ገንዘብ እንደሚባክን ጨምረው አጋልጠዋል፡፡

ወያኔ ለዚህ አላማው ማሳኪያ ይሆነው ዘንድ በአዲስ አበባ 300 ሺህ ተወዳዳሪ እጩዎችን አቅርቢያለሁ እያለ እየለፈፈ ሲሆን፣ ተቃዋሚዎች 32ሺህ እጩ ተወዳዳሪዎችን ማቅረብ እንደሚችሉም እየገለፀ ይገኛል፡፡

በተለይም በአሁን ሰዓት ሕዝቡ የሚቀምሰው ወቅት በጠፋበት ወቀት አስቀድሞ ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች ሊሟሉለት ሲገባ ወደ ምርጫ ለመግባት መሯሯጡ ያለውን የስልጣን ጥማት በግልፅ የሚሳይና የማያስረዳ መሆኑን የጠቆሙት አንድ የተቃዋሚ አባል ሕዝቡ በምርጫ 97 የደረሰበት በደልና ብሶት ሳይሽር አሁን ወደ ምርጫ ለመግባት የሚደረገው ሩጫ ተገቢ አለመሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

የኦፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በበኩላቸው አዲስ አበባ በኦሮሚያ ወረዳዎች የተከበበች በመሆኗ ፊንፊኔ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ነች ተብሎ በሕገመንግስቱ ላይ የሰፈረ በመሆኑ በዚሁ ሕግ መሠረት ከኦሮሚያ ለሚመጡ ተመራጮች በአዲስ አበባ ምክር ቤት በቂ ወንበር ሊሰጣቸው ይገባል በሚል

ሐሳብ ያቀረቡ ቢሆንም የወያኔው ተላላኪ ሆድ አደሩ ሽፈራው ጃርሶ የኢትዮጵያዊነትን ክብር በሚነካ መልኩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳን ያንጓጠጣቸው ሲሆን እሳቸውም ይህን ከሰሙ በኋላ ከም/ቤት ስብሰባውን አቋርጠው መውጣታቸውን ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡

ለዘመናት በቅርስነት ተመዝቦ የተቀመጠው ጥንታዊ ቅርሶች በአባ ገ/መድህን ትዕዛዝ ወደ አክሱም እንዲጓጓዝ መደረጉ ተጋለጠ፡፡

ሕዳር 21 ቀን 2000 ዓም በአክሱምከተማ የማሪያም እለት የሚሊኒየም በዓል ይከበራል በሚል በአባ ገ/መድህን ትዕዛዝ በየቤተክርስቲያኑ ያሉ ቅርሶች ተሰብስበው ወደ አክሱም እንዲሄዱ መደረጉ የሐገሪቷን ቀርሶች ለመዝረፍ ሆን ተብሎ ታቅዶ የተሰራ መሆኑን የገለፁት የቤተክህነት ምንጮች ከዚህ ቀደም ከየቤተክርስቲያኑ ያሉ ቅርሶች ለመውሰድ ብዙ ሙከራ ተደርጐ ሳይሳካ የቀረ ሲሆን፣ አሁን ግን በሚሊኒየም በዓል ምክንያት ተደርጐ በየቤተክርስቲያኑ ያሉት ቅርሶች ተጠራርገው ወደ አክሱም መወሰዱ አሳዛኝ እና ቅርስ ዝርፊያ እንደሆነ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

ምንጮቹ አክለውም የአክሱም ማሪያም በየዓመቱ የሚከበር በዓል መሆኑ ይታወቃል ዘንድሮ ግን የሚሊኒየም በዓል ተብሎ በአዲስ አበባ አድባራት ያሉትን ቅርሶች በሙሉ ወደ አክሱም መውሰድ እስከዛሬ ለመዝረፍ ምክንያት ጠፍቶለት የነበረውን አሁን ግን በግላጭ ያለ አንዳች ከልካይ በአባ ገ/መድህን ትዕዛዝ ቅርሶች ሁሉ ወደ አክሱም ተጭነው ተወስደዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አዲስ አበባ ያሉት ደብሮች ባዶ ሆነዋል ሲሉ በቁጭት ገልፀዋል፡፡

ከአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ በየቤተክርስቲያኑ ተከብረው ተቀምጠው የነበሩት ቅርሶች ወደ አክሱም ከተወሰዱ በኋላ በምትካቸው የተወሰዱትን የሚመስሉ ነገር ግን ሐሰተኛ ቅርሶች ተሰጥቶ እንደሚመለስ ምንጮቹ ያላቸውን ሥጋት ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ ቀድሞ በወርቅ የተሰሩ መስቀሎች ከአዲስ አበባ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አባ ገ/መድህን ይሰጠኝ ብለው ቢጠይቁም በወቅቱ የነበሩት የደብሩ አለቆች የሕዝብ ንብረት በመሆኑና ቅርስ ስለሆነ አንሰጥም በማለት ውዝግብ ውስጥ ገብተው የነበረ ቢሆንም ጥያቄው ከቀረበ ከጥቂት አመት በኋላ የደብር አለቆችን አንስተው ወደ ሌላ ቦታ ካዛወሩ በኋላ የአባ ገ/መድህን ሰዎች ተተክተው የወርቅ መስቀሉ ለአባ ገ/መድህን እንደተሰጠ ያስታወሱት ምንጮች አሁንም ወደ አክሱም የተጓዙት ቅርሶች ይመለሳሉ ብሎ መጠበቅ እሳት ላይ እንደወደቀ ቅቤ መቁጠር ነው ሲሉ ያላቸውን አስተያየት በሐዘን ይገልፃሉ፡፡

ከወያኔ ካድሬዎች በላይ ለወያኔ ቡድን እያገለገሉ ያሉት አባ ገ/ሙድህን ሰሞኑን ፎቷቸው በየቤተክርስቲያኑ እንዲሰቀል መመሪያ ማስተላለፋቸው ታወቀ፡፡

የእምነቱ ተከታዮች በሚሰጡት እርዳታ በየቤተክርስቲያኑ በርካታ የንግድ ሱቆች ተገንብተው እየተከራዩ ቢሆንም ገቢው ግን ለአባ ገ/መድህን መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ አሁን ደግሞ የሚያደርጉት ነገር ሲያሳጣቸው በየቤተክርስቲያኑ በር ላይ በትልቅ ፖስተር ተሰርቶ ፎቷቸው እንዲሰቀል ትዕዛዝ በመስጠታቸው በሁለት ደብሮች ተሰቅሎ እንደሚገኝ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ደሀው የእምነቱ ተከታይ ለቤተክርስቲያን እያለ ከአፉ ነጥሎ በሚሰጠው ምፅዋት እየተንደላቀቁ ያሉት እነ አባ ገ/መድህን የሚያደርጉት ጠፍቷቸው እንደ ደርግ ሊቀመንበር ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማሪያም ፎቷቸው በየአደባባዩ እንዲሰቀል ትዕዘዝ መስጠታቸው ወትሮም የእምነት አባት አለመሆናቸው ሲነገር የነበረ ሲሆን አሁንም ይህንኑ አባባል በሚያጠናክር መልኩ በየቦታው «ምስሌ ይለጠፍ» እያሉ በብዙ ሺህ የሕዝብ ገንዘብ ማባከናቸው በአለማዊ ነገር የሚጨነቁና የነፍስ አባትነት በውስጣቸው ቅንጣት ታህል የሌላቸው መሆኑን በገሀድ ያስመሰከሩበት ወቅት ነው ሲሉ እነዚሁ ምንጮች አብራርተዋል፡፡

ዛሬ በርካታ የእምነቱ ተከታዮች የሚልሱት የሚቀምሱት አጥተው በየቤተክርስቲየኑ ደጃፍ ተኮልኩለው ውለው እያደሩ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔው ቀንደኛ ካድሬ አባ ገ/መድህን አለማዊ የሆነውን ሥራ ለማከናወን ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ማድረጋቸው የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲሉም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ በአራት ኪሎ የሚገኘው የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች አስተዳደራዊ በደል ተፈፀመብን፣ በሙስና የተጨማለቁ የኮሌጅ አስተዳደሪዎች ለፍርድ ይቅረቡ ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው ትምህርት ቤቱ ተዘግቶ በርካታ ተማሪዎች ወደየ የመጡበት እንዲመለሱ ተደርጐ «ምርጥ» የተባሉ የራሳቸው ወገኖች ብቻ ቀርተው እንደሚገኙ የገለፀት ምንጮች የፀረ ሙስና ኮሚሽን ተብዬው ሙስና ማጥራት ሌላ መ/ቤት ከሚሄዱ ቤተክህነት ቢጀመር ከሰውየው ጀምሮ ተያያዥ የዘር ሐረግ ያላቸው በሙሉ ዘብጥያ በወረዱ ነበር፡፡ ግን ንጉስ አይከሰስ በሚል ብሂል የሚነካቸው ስለሌለ የሕዝብን ሐብትና ንብረት እንደልባቸው እያፈሱ የግል ድርጅት አቋቁመው እያስነገዱ ይገኛሉ፡፡ ይህ ከአንድ የእምነት አባት ነን ከሚል ሰው የማይጠበቅ ወራዳ ተግባር ከመሆኑም በላይ እምነቱን ማራከስ ነው ሲሉም ምንጮቹ በቁጭት ይገልፃሉ፡

የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ መርማሪዎች በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ቅሬታ ማሰማታቸውን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ፡፡

እንደ ምንጮቹ ዘገባ ከሆነ ከሕዳር 19 እስከ 21 ቀን 2000 ዓም ድረስ በአዲስ አበባ የፌዴራል እና የአዲስ አበባ ፖሊስ መርማሪዎች አሙዲአስ የተባለው ለወያኔ

ቅርበት ያለው ድርጅት ባዘጋጀው ትምህርት ላይ እንደገለፁት እስከዛሬ ድረስ በስህተት ሲሰሩና ሕዝብን ሲበድሉ እንደነበር አምነው ይህንን ስህተት ሊሰሩ የቻሉት ደግሞ የወያኔ ቡድን በሚሰጣቸው መመሪያ እንደነበረ አምረረው ሲገልፁ መደመጣቸውን ገልፀዋል።

ለ3 ተከታታይ ቀናት በተሰጣቸው ትምህርት ላይ ማንኛውም ተጠርጣሪ ቃሉን መስጠት ካልፈለገ መብቱ አንደሆነ ተገልፆላቸው እስከዛሬ እንዲህ የሠራ አለወይ? ተብለው ከመምህራኑ የተጠየቁ ሲሆን፣መርማዎቹም «እኛ ምርመራ የምናካሂደው በዱላ በመደብደብና በማሰቃየት እንጂ የሙያ ብቃት ተመርኩዘን አይደለም» ካሉ በኋላ በተለይ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ነው ከተባለ እንደ ጭራቅ ተቆጥሮ ከፍተኛ ድብደባ እንደሚፈፀምበትና ያለውድ በግድ ያልሰራውንና ያላየውን ሐሰተኛ ቃል ተቀብለን ነበር ለሚመለከተው ክፍል የምናስተላልፈው ይህ ደግሞ ሊሆን የቻለው ከበላይ ሆነው የሚመሩን አለቆቻችን ትዕዛዝ በመሆኑ ነው ሲሉ አስተያየት ሲሰጡ እንደነበረ ምንጮቹ ገልፀው ለዚህ ሁሉ የዳረጉን ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣን ናቸው እያሉ አለቆቻቸውን ሲወነጅሉ ተደምጠዋል።

በአመለካከቱ የወያኔ ቡድን ተቃራኒ በመሆኑ የሰው ልጅ እንደ አውሬ እየተቀጠቀጠ ያልሰራውንና ያልፈፀመውን ቃል ይሰጥ እንደነበረ የገለፁት መርማሪ ፖሊሶቹ አሁን ግን በዚህ ወቀት ለምን ይህን ትምህርት እንድንማር ለምን አስፈለገ? ሲሉም ይጠይቃሉ።

የወያኔ ቡድን እንደ ድፎ ዳቦ ከውስጥና ከውጭ እየተለበለበ ባለበት በዚህ ፈታኝ ወቅት መርማሪ ናቸው የተባሉትን የራሱን ፖሊሶች ይህንን መሰል ትምህርት መስጠቱ ለአለም አቀፍ ድርጅቶች ማሳያ እና ገንዘብ መለመኛ ሊያደርግ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በሌላ በኩል ፖሊሶች ወደ ኋላ መለስ ብለው የሰሩትን ግፍና ሥቃይ እንዲያዩ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ በሰሩት ግፍ ተጠያቂ መሆናቸው እንደማይቀር ቁልጭ ብሎ እንዲታያቸው ታስቦ የተደረገ ነው ሲሉም ምንጮቹ ይገልፃሉ።

በመጨረሻም ለብዙ ዓመታት የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞችን ማህበር ለማፍረስ ከበረከት ስምኦን ጋር ሆኖ ሲዳክር የነበረው መ/አለቃ ወንደወሰን መኮንን የተባለው ግለሰብ አሁንም ወያኔ ያረቀቀው የፕሬስ ሕግ እንዲፀድቅ ለማድረግ ውስጥ ውስጡን ከበረከት ስምኦን ጋር እየሰራ መሆኑ ተጋለጠ።

ይኸው ለሆዱ ሲል ብቻ የኢነጋማ አባላትን ያለ ሐጢያታቸውና ባልሰሩት ስራ ለወያኔው ባለሥልጣን በረከት ስምኦን እያሳበቀ በርካታ ጋዜጠኞችን ለእስር የደረጋቸው ግለሰብ እስከ ዛሬድረስ በሰራው ወራዳና አሳፋሪ ተግባር ሳይሸማቀቅ ይባስ ብሎ የሐገሪቷን ሕዝቦች የመናገር ነፃነት የሚያሳጣውን የፕሬስ ሕግ እንዲፀድቅ

ለማድረግ ከበረከት ጋር በመሆን ብዙ ሺህ ብር ተመድቦለት ሥራ አጥተው የተቀመጡና የወያኔ ቡድን እያሳቃያቸው ያሉትን ጋዜጠኞች በገንዘብ ለመደለል በስብሰባው በረቂቅ ሕጉ ውይይት ላይ እንዲገኙ ለማድረግ እየተሯሯጠ መሆኑን በቅርበት የሚያውቁት ሰዎች ገልፀዋል።

የደቡብ አፍሪካ ባለሙያዎች ያጠኑት የፕሬስ ሕግ አለም አቀፋዊ ይዘት የነበረውና እጅግ ለኢትዮጵያ የፕሬስ እድገት ፈር ቀዳጅ የሚሆን እንደነበረ ጉዳዩን የሚያውቁት ወገኖች ገልፀው የወያኔ በለሥልጣናት በሐገሪቷ ያለው የፕሬስ ውጤት እንዲቀሳቀስ ለማይፈልጉና በሕዝብ ላይ የሚፈፅሙትን በደልና ግፍ ስለሚያጋልጥባቸው ብቻ የታጠናውን ትተው እራሳቸው ያረቀቁትን አፋኝና ጨቋኝ የፕሬስ ሕግ ይዘው መቅረባቸው ታውቋል። ሰሞኑን በዚሁ አፋኝ የፕሬስ ሕግ ላይ ጉዳዩ የማይመለከታቸው ሰዎች ተሰባስበው ጋዜጠኞች መከሩበት ተብሎ በይፋ ሊገለፅ እንደሚችል አንዳንድ የነፃው ፕሬስ አባሎች እየገለፁ ይገኛሉ።

በሌላ በኩል ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ቡድን ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ የሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ከአውሮፓ ሕብረት ጋር የፕሬስ ነፃነትን ለማክበር ስምምነት ፈርሞ 170 ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ያገኘ ቢሆንም እስከአሁን ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ ቅጣት ሊጣልበት ይገባዋል ሲል ገልጿል።

አክሎም የሻዕቢያው ቡድን መሪ ኢሳያስ አፈወርቂም ሆነ ጃሌዎቹ ትናንት በፖርቹጋል ሊዝበን በሚካሄድው የአውሮፓ ሕብረት ሐገሮችና የአፍሪካ መንግስታት መሪዎች ስብሰባ ላይ እንዳይሳተፍ እና እስከመጨረሻውም አውሮፓን እንዳይረግጥ የሚያደርግ ውሣኔ መስጠት አለበት ሲል ገልጿል።